# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## CUSTOMS COMMISSION


ቀን ኅዳር 03 2012
Date

ቁጥር 4/0314/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት</u>፣

ጉዳዩ ፡- <u>የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ላይ ላጋጠሙ ችግሮች የተሰጠ ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 768/2004 እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መሰረት በተሰጣቸው መብት በመጠቀም ለወጪ ንግድ የሚውሉትን ዕቃዎች ለማምረት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ አክሰሰሪዎች፣ ማሽነሪዎችና መጠቅለያዎች አስገብተው የሚጠቀሙበት ቢሆንም የስርዓቱ ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፉን በተገቢው ባለመረዳትና ባለመገንዘብ እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው የማወራረድ ሥራ መስራት ባለመቻላቸው በቅርጫፍ ጽ/ቤቱ አገልግሎትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሶ የመፍተሔ አቅጣጫ እንዲሰጠበት በማለት የአ.አ. ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር 01/ደ43/685 በቀን 13/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮች በማሻሻል በስርዓቱ ላይ የሚያጋጠሙ ችግሮች ከስር መሰረቱ እስኪወገድ ድረስ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና መመሪያዎቹ አፈፃፀም በባለመብቶቹ በኩል የግንዛቤ እጥረት በመኖሩና መንግስት በወጪ ንግድ የተሰማሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ ልዩ ትኩረት አደርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሮቹ መፍተሔ መስጠት አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም የኮሚሽኑ የበላይ አመራር በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት በማድረግ ውሳኔ ያስተላለፈ በመሆኑ በውሳኔው መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ የቃለ-ጉባኤውን 04 ገጽ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሚሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>በያሉበት</u>፣

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች የሚፈቱበት የውሳኔ ሃሳብ ላይ በተደረገ ውይይት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 768/2004 እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መሰረት በተሰጣቸው መብት በመጠቀም ለወጪ ንግድ የሚውልትን ዕቃዎች ለማምረት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ አክሴሰሪዎች፣ ማሸጊያዎች እና መጠቅለያዎች አስገብተው የሚጠቀሙበት ቢሆንም የስርዓቱ ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፉን በተገቢው ባለመረዳትና ባለመገንዘብ እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው የማወራረድ ሥራ መስራት ባለመቻላቸው በቅ/ጽ/ቤቶች እልባት ያላገኙ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮች በማሻሻል በስርዓቱ ላይ የሚያጋጠሙ ችግሮች ከስር መሰረቱ እስኪወገድ ድረስ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና መመሪያዎቹ አፈፃፀም በባለመብቶቹ በኩል የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ እና መንግስት ለወጪ ንግድ የተሰማሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ ልዩትኩረት አደርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሮቹ መፍተሔ መስጠት አስፈልጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽኑ የበላይ አመራር በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት በማድረግ ከዚህ በታች የተመለከተውን ውሳኔ አስተላልፏል፡-

1.1. <u>የማራዘሚያ ጥያቄ ሳያቀርቡ አንድ ዓመት ያለፈባቸው ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ምርት አምርተው ወደ ውጭ የላኩ ድርጅቶችን በተመለከተ፣</u>

እነዚህ ድርጅቶች ምንም እንኳ በህጉ መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ ባያወራረዱም ጥሬ እቃ አስገብተው ምርት አምርተው ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ በመሆናቸው፤ ጥሬ እቃውን እና ምርቱን ለሌላ አላማ ያላዋሉ በመሆናቸው መንግስትን ያሳጡት ጥቅም ባለመኖሩ ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ምርት አምርተው ወደ ውጭ የላኩ ስለመሆኑ ተጣርቶ በህግ የተቀመጠው ጊዜ ያለፈ ቢሆንም የማወራረድ ሥራ እንዲከናወንላቸው እና በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈፅሙ በደብዳቤ እንዲገለጽላቸው፣

1.2. የማራዘሚያ ጥያቄ ሳያቀርቡ አንድ ዓመት ያለፈባቸው ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ምርት አምርተው ወደ ውጭ ያላኩና ያልተጠቀሙት ጥሬ እቃ ያላቸው ድርጅቶች በተመለከተ፣

እነዚህ ድርጅቶች በዚህ ሁኔታ ያመረቱትን ምርት በጊዜው ወደ ውጭ መላክ ያልቻሉበት የተለያዩ ምክንያቶች ያላቸው ሲሆን ምርቱ ወይም ጥሬ ዕቃው በመጋዘን መኖሩ ተረጋግጦ እና ያልተላከበት ምክንያት ከሚመለከተው ከሚመለከተው መ/ቤት ማስረጃ ሲያቀርቡ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከቅ/ጽቤቱ ጋር ስምምነት በመግባት አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርቱንወደ ውጭ እንዲልኩ ተደርጎ የማወራረድ ሥራ እንዲሰራ፤

በሌላ በኩልበምርት ግብዓትነት ያልዋለው ጥሬ እቃ የወጪ ምርት ለማምረት የጥራት ችግር የሌለበት ከሆነ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት አምርተው ወደ ውጭ እንዲልኩ ሆኖም ግን ጥሬ እቃው የጥራት ችግር ያለበት ከሆነ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ በማድረግ የኮሚሽኑ ሰራተኛ በተገኘበትእንዲወገድ ተደርጎ በተወገደው መጠን በማወራረድ ጊዜ ከግምት ውስጥ እንዲገባ እና በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጽሙ እና ኃላፊነት እንዲወስዱ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፡፡

1.3. የማራዘሚያ ጥያቄ ሳያቀርቡ አንድ ዓመት ያለፈባቸው ሙሉ ጥሬ እቃዎች ወደ ምርት ሳይለወጡ በእጃቸው ላይ ያለ ድርጅቶች በተመለከተ፤

እነዚህ ድርጅቶች ባስገቡት ጥሬ እቃ በጊዜው በማምረት ወደውጪ መላክ ያልቻሉበት የተለያዩ ምክንያቶች ያላቸው ሲሆኑ ጥሬ እቃዎች በመጋዘን መኖራቸው ተረጋግጦ እና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶ ወደ ውጭ ያልተላከበትን ምክንያት ከሚመለከተው መ/ቤት ማስረጃ ሲያቀርቡ ይህ ውሳኔ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮበአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጥሬ እቃውን በመጠቀም ምርት አምርተው ምርቱን ወደ ውጭ እንዲልኩ እንዲደረግ እና የማወራረድ ሥራ እንዲከናወን፤ እቃው የጥራት ችግር ያለበት ከሆነ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ በማድረግ የኮሚሽኑ ሰራተኛ በተገኘበት እንዲወገድ ተደርጎ በተወገደው መጠን በማወራረድ ጊዜ ከግምት ውስጥ እንዲገባ እና በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጽሙ እና ኃላፊነት እንዲወስዱ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፡፡

Ethiopia Customs Commission
Records Documentation

1.4. <u>የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ምርት አምርተው በመሸጥ የማወራረድ ስራ ተከናውኖላቸው ክፍያ ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኃላ ከሚመለከተው መ/ቤት አዲስ የግብአት ምርት ጥምርታ አሻሽለው የሚያቀርቡ ድርጅቶችን በተመለከተ፤</u>

የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ወደ ሀገር ያስገቡትን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ምርቱን አምርተው ወደ ውጭ የላኩ ሆኖ ነገር ግን የተጠቀሙትን ጥሮ ዕቃዎች በሀገር አቀፍ ስታንደርድ ግብዓት ምርት ጥምርታ ባለማፀደቃቸው ቀደም ሲል ያስፈቀዱትን የተተካከ፣የመለኪያ ለውጥ፣ የተጨማሪ ግብዓት፣ የጥምርታ ማስተካኪያዎችን ቀረጥና ታክስ ከነቅጣት ከተወሰነባቸው በኃላ በማቅረባቸው ውድቅ የተደረገባቸውን ድርጅቶች በተመለከተ፣

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ጠቃሚ ድርጅቶችን የግብዓት ምርት ጥምርታ፣ የግብዓት ምርት ጥምርታ ማሻሻያ የማድረግ፣ የግብዓት እና ምርት ተተካኪ የማጽደቅየተተካኪ፣የመለኪያ ለውጥ፣ የተጨማሪ ግብዓት አጽድቆ ለጉምሩክ የማሳወቅ ስልጣን በቀድሞው ስሙ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአሁኑ ስያሜው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር እንደሆነ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ አዋጅ ቁጥር 768/04 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣ የብሄራዊ ግብዓት ምርት ጥምርታ መመሪያ የተደነገገ ስለሆነ እና ሚ/ር መ/ቤቱ ከአምራች ላኪው የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ በየደረጃው በማጣራት ጥያቀው አሳመኝ መሆኑን በመግለፅ በህጋዊ ደብዳቤ ለኮሚሽኑ እስካሳወቀ ድረስ የማወራረድ ስራው ከተከናወነ በኂላ የቀረበ ውሳኔ ቢሆንም ኃላፊነት ከተሰጠው መ/ቤት የቀረበ ውሳኔ ስለሆነ ከማስተካከያ በፊት በተከናወነ የማወራረድ ስራ የተጠየቀ ቀሪ ሂሳብ ውድቅ ተደርጎ በማስተካከያው መሰረት የማወራረድ ስራ እንዲከናወን፤

1.5. <u>በወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ጥሬ እቃ አስገብተው በማምረት ምርቱን ወይም ጥሬ እቃውን ባለበት ሆኔታ አገር ውስጥ የሸጡ ድርጅቶችን በተመለከተ፤</u>

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 10/3 መሰረት በቫውቸር ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርቱ ተመርቶ ወደ ውጭ ገበያ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ድርጅቶች ከውጭ ያስገቡትን ጥሬ እቃ ለታለመለት አላማ ያላዋሉ ስለሆኑ በህጉ መሰረት ላስገቡት ጥሬ እቃ ቀረጥና ታክስ ከነቅጣቱ እንዲከፍሉ እንዲደረግ፤

1.6. <u>የቦንድድ ግብአት አቅርቦት መጋዘን ስርአት ተጠቃሚ ሆነው ጥሬ እቃ አስገብተው በአንድ አመት ውስጥ ለአምረቾች ያላስተላለፉ እና ማራዘምያ ያልጠየቁ ድርጅቶችን በተመለከተ፤</u>

እነዚህ ድርጅቶች ጥሬ እቃው ለአምረቾች በጊዜው ማስተላለፍ ያልቻሉበት የተለያ ምክንያቶች ያቀረቡ ሲሆኑ ጥሬ እቃው በመጋዘናቸው መኖሩ ተረጋግጦ እና ለአምራቾች በጊዜው ማስተላለፍ ያልቻሉበት ምክንያት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማስረጃ እንድያቀርቡ በማድረግ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀንጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጥሬ እቃውን ለአምራች ላኪዎች እንዲያስተላልፉ ጥሬ እቃውን የሚያስተላልፉት ለአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ከሆነ ግን ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከነቅጣቱ ከፍለው በአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቁ ተደርጎ የማወራረድ ሥራ እንዲከናወንላቸው፤ ሆኖም በእጃቸው ላይ ያለው ጥሬ እቃ የወጪ ምርት ለማምረት የጥራት ችግር ያለበት ከሆነ ከሚመለከተው የመንገስት አካል ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ በማድረግ የኮሚሽኑ ሰራተኛ በተገኘበት እንዲወገድ በተወገደው መጠን በማወራረድ ወቅት ከግምት እንዲገባ እንዲደረግ ሆኖ በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጽሙ እና ኃላፊነት እነዲወስዱ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እነዲሰርሳቸው እንዲደረግ ፡፡

1.7. <u>በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ በመሆን ሲሰሩ ቆይተው የተሸጡ እና ፈቃዳቸው የተቋረጠ ድርጅቶች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ቀርበው ያላወራረዱ እና አወራርደው ክፍያ ያልጀመሩ ድርጅቶች በተመለከተ፡፡</u>

በአዋጅ ቁጥር 768/2004 ድንጋጌዎች መሰረት ቀርበው የቫውቸር ሰነድ ባላወረረዱት ላይ ተገቢው ክትትል በማድረግ እንድያወራርዱ እንዲደረግ ቀርበው ካላወራረዱ ስርዓቱን በመጠቀም ወደ አገር ያስገቧቸውን ጥሬዕቃዎች እና ምርት አምርተው ለውጪ ገበያ የላኩ ስለመሆናቸው በስማቸው ዲክለር የተደረጉ የገቢ እና ወጪ ዲክለራሲዮኖችን ከጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና ከጉምሩክ የመረጃ ቴክኖሎጂ(አሲኩዳ እና የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት) ሰነዶችንና መረጃዎችን በማጣራት የማወራረድ ስራ እንዲከናወን ውጤቱን መሰረት በማድረግ ከድርጅቶች የሚፈለግዕዳ ያለ እንደሆነ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ እንዲደረግ፤ አወራርደው ክፍያ ያልጀጀመሩት ደግሞ ክትትል ተደርጎባቸው የሚፈለግባቸው ዕዳ ቀደም ሲል በተጠየቁት መሰረት ከፍለው እንዲያጠናቅቁ እንዲደረግ፤ ሆኖም ድርጅቶች ከመሸጡ እና ፈቃዳቸው ከመቋረጡ በፊት በህጉ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ጥሬ እቃ አስገብተው አምረተው ለውጭ አገር ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ያስገኙ ካሉ በተ.ቁ 1 ውሳኔ መሰረት ቫውቸራቸው እንዲወራረድላቸው እንዲደረግ፡፡

በአጠቃላይ በወጪ ንግድ ማበረታቻ ስርዓት አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን የአምራች ላኪዎችን ከመደገፍ አንፃር እና የመንግስትኝ ጥቅም ከማስከበር አኳያ በአግባቡ በመቃኘት የኮሚሽኑ የበላይ አመራር የወሰነው ውሳኔ በጥንቃቄ እንዲፈፀም በሸኝ ደብዳቤ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡